የምፅዓቱ መፅሐፍ ቅዱስ HOLY BIBLE የምሥራች

|ቅጽ 84 ቁጥር 4(982)|

“እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን” (የሐዋርያት ሥራ 6፥4)

ቅዱስ ቃሉና ጸሎት!

(በእንድሪው ሙሬ/ Andrew Murray)

“በእኔ ብትኖሩ ቃሎቹም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል” ዮሐንሰ 5፡17

የእግዚአብሔር ቃልና የጸሎት ሕይወት ማንነታችንን ይወስናል። እግዚአብሔር ምንም አቻና ገደብ የሌለው በሁሉ ላይና በሁሉም ሥፍራ ሙሉ ሥልጣን ያለው ነው።

እግዚአብሔር የተሰፋ ቃሎቹን የሚፈጽም ኃይሉንና ቅድስናውን በፈለገበት ሁኔታና ጊዜ ሊገለጽ የሚችል ሁሉን ቻይ ጌታ ነው።

እግዚአብሔር በቃሉ በቅዱሳት መጽሐፍት በተጻፉልን ይናገራል ህይወትና ቅድስናን ከኃይል ጋር ያጎናጽፋል። “እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው” (ዮሐንስ 6፡63)

መናገር የማይችለው እንዲናገር መሰማት ያልቻለው እንዲሰማ እንደ ልጆች እርሱን እንዲቀበሉት ማድረግ የሚችል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

በመንፈስ በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በማይታሰብ መልክ ቅዱስ መንፈሱን እያፈሰሰብን እራሳችን ተፈትተን ሌሎችም የሚፈቱበትን ኃይል እንቀዳጀለን። የእግዚአብሔር መንፈስ የማይሰማውን የሰዎች ጆሮና ህሊና በመክፈት የእግዚአብሔርን እውነት እንዲሰሙና እንዲቀበሉት ያስችላል:: (ኢሳይያስ 50፡4)

ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚኖረን በቅዱስ ቃሉ በተሞላ የጸሎት ሕብረት ነው።

የእግዚአብሔር ቃልና ቅዱስ መንፈስ የጠጠረውን የሰው ልብ ሰብሮ ቅድስናን ያለብሳል ኃጢያትና እርምን ሁሉ ጠራርጎ ያስወግዳል።

ጌታችን በእኔ ብትኖሩ በማለት በሰጠን ተስፋ በሁለመናችን በአእምሯችን በድርጊታችን በእግዚአብሔር ታምነን ተደግፈን መኖር እንድንችል ነው። በዚህ ሁኔታ ከጌታ ጋር ሕብረት ሲኖረን የለመነውን ሁሉ ጌታ ይሰጠናል። ጌታ የሚሰጠንም እንደፈቃዱ በሆነው እርሱን በሚያስከብር ጉዳይ ላይ ይሆናል። የብዙዎቻች የጸሎት ሕይወት የማንነታችንና የገጠሙን ሁኔታዎች ነጸብራቅ ነው። ጌታ ማለፍ ያለበት ነገር ካለም ለእኛ ጸሎት ያልተመለሰ ቢመስለንም የጌታ ሀሣብ በዚያ ዝምታው ቢሆንም ይፈጸማል።

እግዚአብሔር የነገድ አባት ተብሎ በሚታወቀው አብርሃም ሕይወት ይህንን ከእርሱ ጋር መጣበቅ የጸሎት መልስና የተሰፋ ቃል መፈጸም ያስተምረናል:: (ዘፍጥረት 12፡4)

ጌታ እግዚአብሔር እንደቃሉ እየኖርን ለግላችን ለቤተሰባችን ለሀገራችንና ለመላው ዓለም መፍትሔ የሚያመጣ የፀሎትና የቃሉ ሕይወት ይሰጠን - አሜን።

የእግዚአብሔር ቃል ለግላችን የተሰጠ የጌታ ሰጦታ ነው

(በአሣታሚው በሪች ካርማይክል/Rich Carmichael/)

የዚህን ወር እትም ለማዘጋጀት በምተጋበት ሰዓት የወንጌል ሚሰዮናዊ ሜሪ ሞንሰን ያቀረበችውን ምስክርነት እያነበብኩ በመንፈሳዊ መነቃቃት ተሞላሁ።

የእግዚአብሔር መንፈስ በታሪክ ሰዎችን የሚያነቃቃውና የሚያድሰው የእግዚአብሔር ቅዱስ ፍርሀት በሰዎች ላይ ከወረደ በኋላ ነው። “እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ አበረታሃለሁ፤ እረዳህማለሁ” (ኢሳይያስ 41፡10)

በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ለነብዩ አትፍራ የሚል መልዕክቱን ከሙሉ ተስፋው ጋር የሰጠው ነብዩ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ባየ ጊዜ “ወዮ ጠፋሁ” ብሎ የተናገረበትን መንፈሳዊ ልምምድና የእግዚአብሔርን ፍርሀት እራሱ እግዚአብሔር ሰለሚያውቅ ነው።

እንደ እግዚአብሔር የሰዎችን ማንነትና ያሉበትን ሁኔታ በሚገባ የሚያውቅ ማንም የለም። እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ አትፍራ አትደንግጥ አበረታሃለሁ ሲለን በእርሱ ታምነን እንድንበረታና እርሱ ያዘዘንን ሁሉ ለመፈጸም እንድንዘጋጅ እንድንገሰግስ አምላክ ቀርቶ ሰጋ ለባሹን ታምነው ከሚሰማሩት በመለየት ነው፡

እግዚአብሔር እንደሚደርሰልን መረዳት ትልቅ ማስተዋል ነው።

እግዚአብሔር እያንዳንዳችን በቅዱስ ቃሉ ባለንበት ሁኔታ ሊገናኘን ይፈልጋል። እርሱ ጌታ እግዚአብሔር ዘወትር ሊረዳን ሊያገለግለንና ካለንበት አስቸጋሪ ሁኔታም ሊታደገን ይችላል። (መዝሙረ ዳዊት 119፡28፣ ዮሐንስ 20፡31)

በሚገጥመን መንፈሳዊ ውጊያ እግዚአብሔር የቃሉን መመከቻ ጋሻና ጦሩን ሰጥቶናል (ኤፌሶን 6፡17)

እግዚአብሔር የሰጠን የዘላለም ሕይወትና የምድር በረከት ሁሉ እጅግ ከፍ ያለ ፍቅሩንና ሰጦታውን ያሳዩናል (ዮሐንስ 3፡16)

በዚህ እትም የእግዚአብሔርን ልዩ ሰጦታ በቅዱስ የወንጌሉ ቃል እንዳገኘን የሚያረጋግጥ ተስፋ ያለን ሲሆን ይህንንም ጠብቀን እንድንገኝ የምንተጋበትን እድል ሰጥቶናል።

በግልም ሆነ በሕብረት በዚህ የጌታ ሰጦታ ተጠቅመን ለበረከት እንሁን።

የእግዚአብሔር ቃል ኃያልነት (በዴሬክ ፕሪንስ/Derek Prince)

“አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደመንገዴ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው። ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ ምድርን እንደሚያረካት ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል” (ኢሳይያስ 55፡8)

እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን መልካም እቅድ ከልቡ ሃሳብ ያካፍላል። እንዲህ እግዚአብሔር በረከቱን እንደሚሰጠን ቃል ከገባልን ለዚህ እንዴት እንመልስ? እግዚአብሔር በረከቱን እንደ እንደሚሰጥ የቃሉ በረከትም በከንቱ ወደ እርሱ እንደማይመለስ ካረጋገጠልን የእኛ ድርሻ ጌታ የሚሰጠንን በረከት ሁሉ በእምነት ልብ መቀበል ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ ወደ እኛ ሲደርስ አእምሯችንን በእግዚአብሔር ቃል በቅዱስ መንፈሱ ተሞልተን በረከቱን ተቀብለን ልንኖርበት ለሌሎች ልናስተናልፈው ይጠበቅብናል።

የእግዚአብሔርን የሰላም መልዕክት በደስተኛ ልብ ተቀብለን በሀሴት ተሞልተን ሌሎችም የዚህ ደስታ ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ መመስከር ይህንን ተስፋውን ማጋራት አለብን።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የፀሎት ምክንያት (በኪም ቡት/Kim Butt/

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው (ዮሐንስ 1፡1)

2. ጸሎት የክርስቶስ ኢየሱስ ተምሳሌት ነው (ማቴዎስ 4፡1)
3. የጥንት ቤተክርስቲያን በጸሎት ኖረዋል (ሐዋርያት 4፡2)
4. ቃሉ የጌታ ተሰፋ ነው (2 ጢሞቴዎስ 3)
5. የእግዚአብሔር ቃል ጸሎትን ይመክራል (ሮሜ 15፡13) (2 ተሰሎንቄ 2፡16)
6. በቃሉ መጸለይ መታመን ይሰጣል ዮሐንስ 15፡7
7. የእግዚአብሔር ቃል የጸሎት ቃል አለው (መዝሙረ ዳዊት 145)
8. የጌታ ቃል ሕይወትን ያድሳል (ዕብራውያን 4፡12)
9. የጌታ ቃል ምንም ስህተት የለውም (መዝሙር 127
10. የእግሒአብሔር ቃል ዘላለማዊ ነው (21፡33)
11. በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ያዋህዳል (መዝሙረ ዳዊት 63፡1)
12. እግዚአብሔር የሚሰማውን ጸሎት እራሱ ይሰጠናል (ሮሜ 10፡17)

ሁልጊዜ በጸሎት ድልና በረከት ይገኛል።

የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው (ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ)

ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው (ማቴዎስ 21፡13)

በእግዚአብሔር ቤት ዋነኛ የሆነው የጸሎት አገልግሎት ተገፍቶ የሰጋዊ ጉዳዮች ሲከናወኑበት ጌታ ተቆጥቶ ገበታ ለዋጮች (ሸቃኞችን) እየገረፈ ማባረሩ የተጻፈልን ቤቱን የጸሎት ቤት እንጂ የሌላ በምድራዊና የሥጋዊ ጉዳዮች ማከናወኛ እንዳናደርግ ለማስተማር ነው።

በቤተክርስቲያን ታሪክ ሁሉ እንደታየው በመጀመሪያ የክርስቶስ ተከታዮች በመንፈስ ቅዱስ እሳት እየተቀጣጠሉ የእግዚአብሔር ክንድ ሲገለጥባቸው ያሳድዷቸው የነበሩት በጌታ ኃይል ተነክተው ምን እናድርግ? ብለው ከጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ የጌታን ሥራ ከቀና መንገዱ ለማስወጣት ሰይጣን የሚልካቸው ገበታ ለዋጮች (ሸቃጮች) በየጊዜው ተከስተዋል ዛሬም በመካከላችን አሉ።

በጌታ ቤት የገበታ ለዋጭ (ሸቃጭ) ተግባር ሰዎችን ከእውነተኛ የጌታ መንገድ በመለየት በሚጠፋ ጉዳዮች ማሰጠመድና ዋናውን የጌታ ቤት ሥራ የሆነውን ጸሎት ማስተጓጎልና ማሰቀረት ነው።

በመንፈሳዊ መነቃቃት በኃያሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተካሄደባቸው ሥፍራዎችን ሰይጣን ቅጥሩ እንደሚያፈርሰበት ስለሚያውቅ ገበታ ለዋጮች (ሸቃጮች) በየጊዜው ያስማራል።

በእነዚያ ትልቅ የጌታ ጉብኝት በተካሄደባቸው ሥፍራዎች ዛሬ እጅግ የሚቀፍ ኢሞራላዊ ድርጊት እንደሚካሄድ ምስክሮች አለን። ከእግዚአብሔር ቃል የሚጣረስ ጋብቻ ትዳር ባህል እየተሰፋፋ የመጣው በገበታ ለዋጮች (ሸቃጮች) ሥራ ነው። ድሮ በቅድስና በታማኝነት ይታወቁ የነበሩ የወንጌል አማኞችና ህብረቶች እጅግ በከፋ የፍቅረ-ነዋይና በኢሞራላዊ ሥራዎች ተሞልተዋል።

መፍትሔው ዛሬም የጌታችን ክርስቶስ ቃሉን ይዘን በመንፈስ ቅዱስ ጅራፍ ገበታ ለዋጮችን ቸርቻሪዎቹን ማሰወገድ ነው።

የምሰጢር ጸሎት እጅግ አስፈላጊነት

(በጸሎት ህብረት አገልጋዮች/Condensed from purpose in prayer/)

“ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው” (ሉቃስ 18፡1)

ይህ ትዕዛዝና ትምህርት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው። ጌታ ዘወትር በምሳሌ የሚያስተምረው ሰዎች ሀሳቡን በቀላሉ

ተረድተው በህይወታቸው እንዲለማመዱ ለማስቻል ነው።

የጸሎት ሕይወት አስልቺና ተሰፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን ብርታት ከተሰፋ ጋር የሚጨምር የተሰፋና የኃይል ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን የምናገኝበት ልዩ መንገድ ነው። እግዚአብሔር በሁሉም ጊዜ ጸሎታችንን ሊሰማ የተዘጋጀ ነው።

የጸሎት ህይወት ከጌታ ጋር ጥምረት ቅርበትና አንድነት የምንፈጽምበት ስዓት ነው።

በጸሎት በምንተጋበት ወቅት አይኖቻችንና ጆሯችን ከምድራዊ ጉዳዮች ላይ ተነስተው በሁሉን ቻይና ሰጭ እግዚአብሔር ላይ የሚያተኩሩበት ጊዜ ይመጣል።

በጸሎታችን የእግዚአብሔር ቃል ሲመራን የእግዚአብሔርን ድምጽ የምናገኝበት ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ለምን እንደምንጸልይ እንዴት እንደምንጸልይ በቅዱስ ቃሉ በድንቅ ይመራናል። (ሮሜ 8፡26)

በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን ኢትዮጵያ የክፋት የጥላቻ መንስዔ የሆነው ኃጢያት ተንሰራፍቶ ያመኑትን ሳይቀር በያዘበት በዚህ ወቅት የጸሎት አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ነው።

ትልቁ ቁም ነገር እንዴት እንጸልይ በምን ጉዳይ ላይ እንጸልይ ከማን ጋር እንጸልይ የሚሉት ናቸው።

ከሁሉ በፊት ጌታ የታይታ ጸሎትን ሰለማይሰማ ጸሎታችን በእውነተኛ ልብ በሚሰጢር በጓዳችን ካቀረብን በኃላ በእምነትና በጸሎት ሽክም ከሚመስሉን ጋር በእውነት በግልጽነት ባለመደባበቅ ርእሶችን እየተለዋወጥን እንጸልይባቸው (ሉቃስ 18፡11፣ ማቴዎስ 6፡5)

ጸሎታችን የሰዎችን ችግሮችና ሚስጢሮች ማባከኛ ካደረግን የእግዚአብሔር ቅጣትን እናገኛለን በሰዎች ኃጢያትም ከተሳለቅን የእራሳችን ኃጢያት ያጠፋናል። (ሉቃስ 13)

ጌታ እግዚአብሔር በቅን መንፈስ ያለመታከት የምንጸልይበትን መንፈሱን ያፍስልን።

በትጋት ስለመጸለይ በቶሬ /R.A. Torrey/

እግዚአብሔር ጆሮ የሚሰጠው በትጋት ለሚደረግ ጸሎት ብቻ ነው። ጌታ የሁሉንም ሰው ጸሎት ቢሰማም እርሱ ሊመልስ የሚፈልገው በትጋት ፊቱን በጸሎት ለሚፈልጉት ነው “እናንተ ትሹኛላችሁ በፍጹም ልባችሁም ካሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ። እናንተም ዘንድ እገኛለሁ ይላል እግዚአብሔር። (ትንቢተ ኤርሚያስ 29፡13)

ብዙዎቹ ጸሎቶቻችን በእግዚአብሔር ምላሽ ያላገኙባቸውን ምክንያቶች ፈትነን ማወቅ መረዳት ይኖርብናል። በጸሎት ርዕሶቻችን ላይ ብርቱ ሸክም ሳይሆን በልማድ ብቻ ወይንም ችግሮች ሰለገጠሙን የምናካሂድባቸው ጸሎቶች ከጌታ መልስ አያገኙም።

በየጊዜው ለምን እንደጸለይን እንዴት እንደጸለይን መች እንደጸለይን ሳናሰተውል የምናካሂደው ጸሎት የትጋታችንን ደረጃ ይገልጻሉ።

ለምንጸልይባቸው ወይም ወገኖች ለሚሰጡን የጸሎት ርእሶች በእውነተኛ ልብ ሸክም ተሰማምቶን ልንተጋባቸውና ያለማቋረጥ ልንጸልይባቸው ያሻል።

ጌታ የትጋት ጸሎት ምሳሌ ያደረገው ለክፉ ዳኛ ሳትታክት ጥያቄዋን ያቀረበችውን ሴት ሲሆን የእኛ የጸሎት ትጋትም ጸሎትን ሊመልስ ለሚችለው ጌታ በሙሉ ትጋት መሆን ይኖርበታል። (ሉቃው 18፡4)

የጸሎት ትጋት የመንፈሳዊ ውጊያ ዋና አካል ነው። መንፈሳዊ ውጊያ ከሰዎች (ስጋና ደም) ሳይሆን ከክፉ የመናፍስት አሰራር ጋር እንደሆነ ሁሉ በጸሎታችን የምናካሂደው ፍልሚያና ትጋትም

የክፉ መናፍሰትን ቅጥር በመሰበር የታሰሩት እንዲፈቱ የተማረኩ እንዲለቀቁ በሚያበቃ ትጋት ነው። (ወደ ኤፌሶን 6፡12)

የእግዚአብሔር ቃል በጸሎት የሚተጉ ሰዎችን በግልጽ ያሰቀምጠል ለእኛም ምሳሌ እንደሆኑን ያስተምረናል (ቆላሲያስ 4፡12)

የትጋት ጸሎት የሚካሄደው በሰዎች ሰሜታዊ ድርጊቶች ሳይሆን ሰሜቶችን በልዩ ሁኔታ በሚያፈልቅ የሚቆጣጠር አእምሮንም የሚገዛ እንዴት የጸሎት ርእሶቶችና ጥያቄዎች እንደሚቀርቡ በሚቀሰቅሰው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚካሄድ ነው። (ሮሜ 8፡26)

ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ በእውነተኛ ትጋት እንድንጸልይ ይርዳን አሜን!

የመንፈሳዊ መነቀቃት ጸሎት (በጆን ዌስሌ /John Wesley/)

በ17ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከዚያም በቀደመው በ15ኛው ክፍለ ዘመን መንፈሳዊ ተሀድሶና መንፈሳዊ መነቃቃትን ያስከተሉ የጸሎት እንቅስቃሴዎች በአውሮፓ ተከሰተዋል በአሜርካም ተሰፋፍተዋል። መንፈሳዊ ተሃድሶ ቤተክርስቲያን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድ እንድትመለስ በፍትሃት ክፍያ ሰዎች ከገሃነም እንደማይተርፉ የሰው ዘር ከኃጢያት ቅጣት የዘላለም ሞት የሚድነው በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መሆኑን የጀርመኑ የቀድሞው መነኩሴ ማርቲን ሉተር አስተምሯል።

በማርቲን ሉተር ሰብከት ሕይወቱ የተለወጠው የእንግሊዙ ሰባኪ ጆን ዌስሌ ደግሞ በመንፈሳዊ መነቃቃት ከአውሮፓም አልፎ በሰሜን አሜሪካ ታላላቅ መንፈሳዊ መነቃቃቶች እንዲከሰቱ ጌታ የተጠቀመበት በልዩ የጸሎት ህይወት ነበር። የዌስሌ የ18ኛው ክፍለዘመን የመንፈሳዊ መነቃቃት ጉዞው የአሜሪካ ነባር ህዝቦች ቀይ ህንዶች የተባሉት ቢሆንም በጆን ዌስሌ የሚሰዮን ጉዞ አያሌ የአሜሪካንና የአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ኃይል የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ የተገለጠባቸው በብርቱ የጸሎት ህብረቶች አገልግሎት ነበር።

ጆን ዌስሌ ለታላቁ መንፈሳዊ መነቃቃት Great Awakening የበቃው በእግዚአብሔር ቃል የሰዎች መዳን በመቀደስ ብቻ ነው በሚል ምሪት ነበር። (1 ዮሐንስ 3፡9፣4፡19) (santification)

በዛሬው ወቅት ግን እነዚያ ታላላቅ የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ የታየባቸው በዌስሌና የሉተራን ማህበሮችና ወንጌላዊያን በሚል የሚጠሩት በአብዛኛዎቹ ከመጸሐፍ ቅዱስ መርህ በሚጣረስ ልምምድ ውስጥ ሰለገቡ የሁላችንንም ጸሎት ተርጓሚው እጠይቃለሁ።

ምንም እንኳን በማህበራዊ ጉዳዮችና ለሰዎች መብት ቢተጉም ከቅዱስ ቃሉ ባፈነገጠ ትምህርት ከማንም ማህበር ጋር ህብረት ሊኖረን አይገባም። “እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ።” (2 ጴጥሮስ 3፡18)

የታማኝ የጸሎት ሚሰዮናዊ ምስክርነት (ማሪ ሞንሰን/Marie Monsen/)

ሜሪ ሞንሰን እግዚአብሔር ለወንጌል ሥራ የተጠቀመባት የኖርዌይ ሚሲዮናዊ ነበረች በ1920 ዓ.ም በሰሜን ቻይና ለተከሰተው የመንፈሳዊ መነቃቃት ሜሪ የመንፈስ ቅዱስ መሣሪያ ሆናለች።

ከአውሮፓ ወደ ቻይና በተጓዘችበት ወቅት በባህር ላይ ወንበዴዎች የታገተች ቢሆንም በጠላፊ ወንበዴዎቹ ለ23 ዓመታት ባገቷት ወቅት ያለማንም ፍርሃትና የበቀል ሰሜት በቅንነት ሰታገለግላቸው በመቆየቷ አያሌ ቻይናውያን

በክፉ ሥራ የተያዙት ሳይቀር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጌታ እየነካቸው በመለወጥ የክርስቶስ ተከታዮች ሆነዋል። ሜሪ በጉዞዋ መጀመሪያ በቻይና ዋና ከተማ በፔኪንግ በመቆየት የማገልገል እቅድ የነበራት ቢሆንም በእንድ የአሜሪካ ሚስዮናዊ ጥያቄ ሻንቱንግ ወደ ተባለ ከተማ በሄደችበት ወቅት አስደናቂ የጌታን ሥራ ከፈጸመች በኋላ በጀልባ በምትጓዝበት ወቅት ለመማረክና ለመታገት በቅታለች ሆኖም ግን እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደሀሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው በሚለው የጌታ ሕያው ቃል ሜሪ እጅግ አስፈሪና አሳሳቢ በሆኑ የባህር ላይ ጠላፊዎች ብትታገትም በጌታ ሰላም ተሞልታ በቆየችባቸው 23 ዓመታት የክርስቶስ የሰላም ልኡክ በመሆን በሕይወትና በቃል ምስክርነት አያሌዎች ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቅ የጌታ ብርሃን እንዲገቡ ምክንያት ሆናለች ። ክብር ለጌታ ክርስቶስ ይሁን!

ለሚስዮናዊ ማሪ የአገልግሎት መሪና የማጽናናት መሪ ቃል ትንቢተ ኢሳይያስ 41፡10 እኔ ከአንቺ ጋር ነኝና አትደንግጭ እኔ አምላክሽ ነኝና አበረታሻለሁ የሚለው የተሰፋ ቃል ነበር።

እምነትን በሚፈታተን በሩቅ ሀገር ለተሰማሩ ሁሉ ይህ የጌታ ተሰፋ ቃል እያበረታታቸው ትልቅ የወንጌል ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ። ጌታ ሰለሰጣው ይክበር!

የጸሎት ሕይወት የዘመናችን ተምሳሌቶች

Lois Stucky and Wesley Dwel (ሎይስ ስተኪና ዌስሌ ዱዌል)

በዚህ ዘመናችን የእግዚአብሔርን ሥራ በጸሎት ተጋድሎ ሲያከናውኑ የምጽዓቱ የምሥራች አስተባባሪ በአሜሪካ ምድር ያገኛቸው በዚህ ወቅት ወደጌታ እቅፉ የገቡ የጌታ አገልጋዮች የምጽአቱ የቦርድ ሊቀመንበር ወንድም ዌስሌ ዱዌልና የምጽዓቱ የምሥራች የእንግሊዝኛው ተባባሪ አርታኢ የነበረች እህት ሎይስ ስተኪ በአገልጋዮችና ተገልጋዮች ዘወትር ሊታወሱ ይኖራሉ።

የእነዚህ ወገኖች ሕያው መልዕክት በዚህ ወር እትም ከእንግሊዝኛው የተተረጎመው የሚከተለው መንፈሳዊ መልዕክት ይገኛል።

በጸሎት ኃያልነት ሰለመቀዳጀት (ዌስሌ ዱዌል 1908-2009)

የድል ጸሎት የሚገኘው በሰው ብርታት አይደለም። እጅግ የተቀደሰ የሚባል ሰው ሳይቀር የድል ጸሎት ያሰከትላል ማለት አይቻልም። ይልቁንስ የድል ጸሎት የሚገኘው በድል አድራጊው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመታመን በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ የእግዚአብሔር ሰጦታ ነው። ይህ የድል ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ መቃተት በደካማው ሰው ውስጥ እንደሚገኝ የአዲስ ኪዳን የጸሎት ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ጽፎልናል።(ሮሜ 8፥26)

የእግዚአብሔር ብቸኛው አማላጅ ራሱም ተማላጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ኃያል ጸሎት የድል ጸሎት እንደሚገኝ ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጣል። (ዮሐንስ 14፥13፣ ሉቃስ 11፡13)

በመንበርከክ የሚገኝ የድል ሕይወት በሎይስ ስተኪ (1920-2006)

“እኔ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ ነኝ፣ በውኑ እኔን የሚያቅተኝ ነገር አለን። (ኤርሚያስ 32፡27)

እንዳች የሚያቅተው ነገር እደሌለ በቃሉ ያረጋገጠው እግዚአብሔር ጸሎታችንን ስምቶ የሚያበረታን አስቀድመን እኛም በእርሱ እግሮች ሥር ስንበረከክ ነው። በረከት -ባራክ-ባሮክ የሚለው ቃል የአማርኛችን መንበርከክ ጥሬ ቃል መነሻ ሴማዊ ቃል ነው። በጌታ እግሮች ሥር በመንበርከክ የድል ጸሎት ሕይወት ይገኛልና። ለምድራችን በጌታ ሥር መንበርከክ ይቀጥል ይስፋፋ አሜን!!

የጸሎት ታላላቅ ጥቅሞች (በጆናታን ኤድዋርድ/Jonathan Edwards/)

በክርስቶስ የሚገኘውን አዲስና ዘላለማዊ ሕይወት የመጠበቅና የማጽናት ጥቅሞች የምናገኘው በብርቱ የጸሎት ሕይወት ነው።

በዚህ ምድርም ሆነ በመጭው ዘላለማዊ ሕይወት እጅግ ጠቃሚ ሕያው ጥቅሞች የሚገኙት በጸሎት ተጋድሎ ነው።

ጌታ በተሰፋ ቃሉ አሰቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሰት ፈልጉ ሌላውም ይጨምርላችኋል የሚለውን የገለጠልን ከምድራዊ ጥቅሞች ጊዜያዊ ከሆኑት በላይ ዘላለማዊውን የከበረውን ጥቅም የክብረ አክሊል ለዘላለም መቀበልን ለማመልከት ነው። (ማቴዎስ 6፡33)

የእምነት ጸሎት የታመመን የሚፈውስ የሞተውንም ሕይወት እንደሚሰጥና እንደሚያሰነሳ ከእግዚአብሔር ቃልና ከቤተክርስቲያን ታሪክ እናገኛለንና ታላቅ ጥቅም ባለው ብርቱ ጸሎት እንትጋ (ያዕቆብ 5፡16)።

የማለዳ ጸሎት (በጄምስ አሌክሳንደር /James Alexander/)

የእለቱን አዲስ ቀን ለሰጠን ጌታ ምንም ሥራና ትምህርተ ወይም የቤተሰብና የሀገር ጉዳይ ቢይዘንም ለእንዲት ደቂቃ ቀኑን ለጨመረልን ጌታ ምሰጋናና ቀኑን እንዲባርክ ሳንጠይቀው ወደ እለቱ ሥራችን መሰማራት የለብንም።

የማለዳ ጸሎት በባህላችን ሰላምታ “ጤና ይስጥልኝ” ብለን ለሰዎች እንደምናቀርበው ጌታ እንኳን በሰላም አሳደርከኝ ተመሰገን ቀኑንም ተረከብ ልንልበት የሚገባ ትልቅ እድል ነው።

ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? (ማርቆስ 8፡36)
እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ሰጥቶን በሁሉ ነገር ተሞልተን ዘላለም ሊኖረን የሚገባውን ነፍሳችንን ማጣት ምን አይነት አሳዛኝ ፍጻሜ ነው ወገኖች እናስተውል። ሁሉን ማትረፍ ብንችልም በሰንፍናችን ልናተርፍ የሚገባው ነፍሳችንን እንዳናጣ የነፍስ ጠባቂ ጌታን በጸሎት እስከፍጻሜ እንማጸነው።

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርዕሶች

ልብን በሚሰብር ሁኔታ የጌታ ተሰፋ በሶሪያ

ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሐዘን እልቂት ሰደት የቤተሰብ መበተን የገጠማት የመካከለኛዋ ምስራቅ ሶሪያ የእግዚአብሔር ተሰፋ እየመጣላት ነው። ለኢትዮጵያውያን የመጀመሪያ የወንጌል መልዕክተኛ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማን) ያፈራችው ሶሪያ በጥቂት አማኝ ልጆቿ ጸሎት ማሳሰቢያዎች ከግማሽ በላይ የተሰደዱ ሕዝቦቿ እየተመለሱ በርሁርህ ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች ርብርብ በመቋቋም ላይ ነች። ጦርነት ያደቀቃት ሶርያን የሚገዙት ባለተረኛ ነፍጥ ታጣቂዎች ቢሆኑም ጌታ ምድሪቱን አልረሳትም እኛም በጸሎት እናስባት በሀገራችን የተሰደዱ ሶሪያዎችንም በፍቅር እንከባከብ እንጸልይላቸው።

ለሰሜን አፍሪካና ለኢራን እንጸልይ

የመጀመሪያዎቹ የክርስቲያን ሰማእታት በካታካምቦ ጌታ የተጠቀመባቸውና በካርቴጅ ትክክለኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅዎች የተጠናቀሩበት ሰሜን አፍሪካ ዛሬ እጅግ የከፋ የወንጌል አማኞች ሰደት ገጥሞታል። የኢራንም የአክራሪነት መንፈስ ያቺን ታሪካዊ ሀገር ሕዝቦች እየጎዳ ይገኛልና በብርቱ ጸሎት እናስባቸው።

የእፋኞችና የወንበዴዎችን የክፋት ሥራዎች በጸሎት እንፋለም

በልዩ ልዩ የዓላማችን ክፍሎች በሀገራችን ኢትዮጵያ ጭምር በሄይቲና በላቲን አሜሪካ ሀገሮች ሰዎች ለመዝረፍ ሴቶችን ለመድፈር የተሰማሩትን እግዚአብሔር እንዲመልሳቸው የሚጠቁ ሰዎችንም እንዲታደግ ለጌታ ጸሎት እናቅርብ ክሰቲያኖች የሰማይና የምድር ዜጋ በመሆናችን ወንጀለኞችን አንተባበር ለታመኑ የጸጥታ ሠራተኞች ጥቆማ እናቅርብ።

በዚህ በሀገራችን ለሚተጋ ለምህረት አምባና ለመሰል ሕገወጥ አስተላላፊዎች ለሚፋለሙ አገልግሎቶች ጸሎትና ድጋፍ እናድርግ በሚቸለንም በፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲሰ አበባ እንደግፋቸው።

በሀገራችን ኢትዮጵያና በመላው ዓለም ሰዎችን በማታለል ለዘመናዊ ባርነት ሰቃይና ሞት የሚዳርገውን ክፉ ሰራ በጸሎት እንደ ህገወጥ አስተላላፊዎችንም እናጋልጥ። እነዚህ ተታልለው ለሰቃይ የሚዳረጉትን እን በሚቻለንም እንዲቋቋሙ እንርዳ፣ እንጸልይላቸው።

የምጽኣቱ የምሥራች ማስታወቂያዎችና ማሳሳቢያዎች

ከማሆኒ ማይጨው (ትግራይ ኢትዮጵያ)
በሕይወቴ እጅግ ጠቃሚ ለሆነው ጋዜጣችሁ ጌታ የተመሰገነ ይሁን። ለብዙ ዓመታት እየተገለገልኩ ለአገልግሎቱ ድጋፍ ሰትጠይቁ ችላ ማለቱ ከብዶኝ የአቅሜን በባንክ ቤት ልኬላችኋለሁ።
ከአስተባባሪው እህታችን በሚያሰፈልገን ወቅት ለላክሽልን ጠቃሚ የገንዘብ እርዳታ እጅግ እናመሰግናለን። ጌታ ክርስቶስ አብዝቶ ይባርክሽ።
ከዚምባብዌ
የምጽዓቱ የምሥራች በናፍቆት የምጠባበቀው ጋዜጣ ነው። ዘወትር እንደደረሰኝ እያነበብኩና ለሰዎች እያካፈልኩት እባረክበታለሁ ጌታ በነገር ሁሉ ይባርካችሁ።

የመዳን ምክሮች

1. ኃጢያተኛ ሰለመሆናቸን ለጌታ እንናሰታውቅ። (ሮሜ 3፥23፣ 6፥23)
2. ልባችንን በነካው በመንፈሰ ቅዱሰ ተመርተን ለኃጢያታችን እንናዘዝ (ኢሳይያሰ 55፡7)
3. ክርስቶሰ ለኃጢያታችን እንደተሰቀለ እንደሞተና እንደተነሳ በማመን በቅርባችን ወዳለ ቤተክርስቲያን በመሄድ ህብረት እንጀምር (ማቴዎሰ 28፡19)
4. በቅዱሰ ቃሉ ያመነውን ለሌሎች እንመሰክር (ሮሜ 10፡9)

ማሳሰቢያ ከአስተባባሪው

የምጽአቱ የምሥራች ጋዜጣን በመተርጎም በነጻ ለወገኖቻችን ሰለማሰራጨታችን ጌታ ይክበር። ይህንን አገልግሎት ለብዙዎች ማድረሰ እንድንችል አገልግሎቱ በጸሎትና በሚቻላችሁ በገንዘብ በመደገፍ የጌታን ሥራ አብረን እንፈጽም።

ኤዲ/አደፍርሰ ሀብቴ መካሻ - አስተባባሪ
(Eddie/Adefris Habte Mekasha/
አሳታሚ ሪች ካርማይካል/Rich Carmichael/
(pulisher)

ሰርጭት፡- ብርሃኑ ጥርሰማ
Distribution Birhanu Tirsema

ሰልክ፡ 0993154034

አዲሰ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

የፖ.ሣ.ቁ /P.O.Box/ 8986
ታይፕና ዲዛይን፡ አቤኔዘር ጽሕፈት ሥራ

አሳታሚ በኢትዮጵያ የምህረት አምባ አገልግሎት

በሶላር ማተሚያ የታተመ

በነጻ የሚሰራጭ